# ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
# Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)

http://www.kinijitethiopia.org
e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

ጋዜጣዊ መግለጫ

ኪል-006/07
የካቲት 5 ቀን 1999

## ታሪካዊ ግዴታችንን በተቀነባበረ ሰላማዊ ተቃውሞ እንወጣ

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ **«ለፍትህ ዘብ መቆም ታሪካዊ ግዴታ ነው»** በሚል አርእስት የካቲት ሁለት ቀን 1999 ያስተላለፈው ህዝባዊ ጥሪ የኢህአዴግ ግትርነትና ጸረ ህዝብ አፈና ውጤት እንጅ፣ ፍትህ የጠማው፣ የህግ የበላይነት የናፈቀው፣ ህዝባችን ፍላጎት አልነበረም:: ለአንድነት ለሰላምና ለዲሞክራሲ የቆሙ፣ የህዝብን ፍላጎትና ምኞት ያስተጋቡ፣ የቅንጅት መሪዎችን፣ ለህዝብ የቆሙ ጋዜጠኞችንና የሲቪክ ማህበረሰብ መሪዎችን፣ በማናለብኝነት በሃሰት ወንጅሎ በፍርድ ስም የፖለቲካ ክስረቱን ለማካካስ በይሉኝታ ቢስነት የመግተርተሩ ውጤት እንጅ የነጻነትና የሰላም ተስፋ የናፈቀው ህዝባችን ፍላጎት አልነበረም::

ህዝብን ንቆ ፣ ህዝብ የመረጠውን ፓርቲ ለማጥፋት መሪዎቹን በእስር ማማቀቅ፣ የህዝብን የዲሞክራሲ መብቶች መጨፍለቅ፣ የኢንፎርሜሽን ፍሰትን ማፈን፣ ዜጎችን በፖለቲካ እምነታቸው ማሳደድ፣ ማፈናቀል፣ ማሰርና መግደል፣ እለታዊ ያሸናፊነት ተስፋ ያስገኝለት መስሎ ታይቶታል:: የህዝብ ዝምታ፣ ታጋሽነትና ጊዜ መስጠት እንደ ፍርሀት፣ እንደሽንፈትና ደካማነት መቁጠር የአንባገነኖች መሰረታዊ ጠባይ ነው:: እምቢ ለሀገሬ፣ እምቢ ለነጻነቴ፣ እምቢ ለመብቴ ብሎ ሲነሳ ግን ሊያግደው የሚችል ሃይል ሊኖር እንደማይችል መገንዘብ በተገባው ነበር::

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ከህዝብ የሚቀርብለትን የፖለቲካ ሰላማዊ ተቃውሞ የአመራር ጥያቄ በትእግስት ቢያዘገየውም የወያኔ/ኢህአዴግ ማናለብኝነት እየጨመረ መምጣቱ አጠቃላይና ቀጣይነት ያለውን የትግል እንቅስቃሴ የታሰሩት የህሊና እስረኞች እስኪፈቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረጉ አማራጭ የሌለው ሆኖአል::

ስለዚህም ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የጾሎትና የትምህርትቤት እንቅስቃሴ በማጠናከር የሚከተሉትን እርምጃዎች ህዝብ እንዲወስድ ማሳሰብ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶአል::

1. የክርስትና እምነት ተከታዮች በቤተክርስቲያናትና አድባራት በብዛት በመገኘት ለታሰሩና ለተሰደዱ ተከታታይ ጸሎት እንድታደርጉ በትህትና እናሳስባለን፣ ይህ ህዝባዊ የጸሎት ስነስርአት እሁድ የካቲት 11 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ወያኔ ኢህአዴግ ለህዝብ ጥያቄ እስከሚገዛ ድረስ እንዲቀጥል እናሳስባለን::
2. የእስልምና እምነት ተከታዮች በመላ ኢትዮጵያ በሚገኙ መስጊዶችና ሌሎች ተመሳሳይ የጸሎት ቦታዎች በመገኘት ተከታታይ ጸሎት እንድታደርጉ በትህትና እንጠይቃለን፣ይህ ህዝባዊ የጸሎት ስነስርአት አርብ እለት የካቲት 9 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ወያኔ ኢህአዴግ ለህዝብ ጥያቄ እስከሚገዛ ድረስ እንዲቀጥል እናሳስባለን::
3. ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በትምህርት ገበታ ላይ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ከሰኞ የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ለአንድ ሳምንት እቤታችሁ እንድትቆዩ እናሳስባለን::
   ሀ. በዚህ አንድ ሳምንት ውስጥ መንግስት ለህዝብ ጥያቄ አወንታዊ ምላሽካልሰጠ አድማውን በመቀጠል ከቅንጅት የሚሰጡትን ተከታታይ መመሪያዎች እንድትጠባበቁ እናሳስባለን::
   ለ. የትምህርት ማቆም በሚደረግበት ጊዜ ሰላማዊ ሰልፍ ወይም በተለያየ መንገድ ለወያኔ/ኢህአዴግ ነፍሰ ገዳይ ቡድን እንዳትመቹ ጥንቃቄ እንድታደርጉ በጥብቅ እናሳስባለን::
4. ባለቤትነታችው የወያኔ/ኢሃዴግና የነሱ ተቀጥላ የሆኑ የንግድና ያገልግሎት ድርጅቶችን፣ ፊልም ቤቶችን ቲያትር ቤቶችንና መዝናኛ ቦታዎችን ጋዜጦችንና መጽሄቶችን መጠቀም እንዲያቆም እናሳስባለን::
5. ሰራተኞች በጤና ተቋማት ከሚያገለግሉ በስተቀር ከሰኞ የካቲት 5 ቀን ጀምሮ በሚሰሩበት ቦታ በመሆን የስራ ማጓተት በመፍጠር እንቢተኛነትን እንዲያሳዩ እናሳስባለን::
6. የወያኔ ፕሮፖጋንዳ መንዥያ ብቻ የሆኑትን የሬዲዮ ጣቢያዎችና ቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ማዳመጥና መከታተል እንዲያቆም እናሳስባለን::
7. የታክሲ ተሽከርካሪዎች በቀን ውስጥ የሚሰሩበትን ሰአት ሩቡን በመቀነስ የአገልግሎቱ መቀነስ እንዲሰማ በማድረግ ተቃውሞአቸውን እንዲያሳዩ እናሳስባለን::
8. የከባድ መኪና አሽከርካሪዎች ፍጥነታቸውን በሩብ በመቀነስ የአገልግሎታቸው መቀነስ እንዲሰማ በማድረግ ተቃውሞአቸውን እንዲያሳዩ እናሳስባለን::

እነዚህ የሰላማዊ ተቃውሞዎች ወያኔ/ኢሃዴግ ያሰራቸውን እንዲፈታ ጫና ለማድረግ በመሆኑ ለአንድ ሳምንት በስራ ላይ ይውላሉ:: እንደሁኔታውና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተከታታይ መግለጫ የምናወጣ መሆኑን እንገልጻለን::

**የተባበረ ትግል ምንጊዜም ያሸንፋል!**

**ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ**

**Kinijit International Political Leadership Secretariat, P.O.Box 14701 Silver Spring MD, 20911 USA**
**Fax / Voice Mail. +1-206-203-3974 www.kinijitethiopia.org**